
جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com



# የዑምራ አፈፃፀምና ህግጋት አጠር ያለ ማብራሪያ

አማርኛ

أمهري

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

شركاء التنفيذ :

دار الإسلام | بيان الإسلام | رواد التراجم | المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص

Tel : +966 50 244 7000
info@islamiccontent.org
Riyadh 13245-2836
www.islamiccontent.org

# የዑምራ አፈፃፀምና ህግጋት አጠር ያለ ማብራሪያ

ምስጋና ሁሉ የአለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። የአላህ ሶላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን። በመቀጠልም፦
ይህ መልዕክት የዑምራን አፈፃፀም፣ ህግጋትና ስነ ስርዓት አጠር ባለ መልኩ የሚያብራራ ነው። በዚህም አንድ ዑምራ አድራጊ በአብዛኛው የሚያስፈልገውን ለማብራራት ጥረት አድርገናል።
አላህን ለተከበረው ፊቱ ጥርት ተደርጎ የተዘጋጀ እንዲያደርግልንና ለመላው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ጠቃሚ እንዲያደርግልን እንጠይቀዋለን።

የኢስላማዊ አስተምህሮቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማህበር የዕውቀት ዘርፍ ኮሚቴ

መግቢያ

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# የመጀመሪያው፡ አምልኮ ተቀባይነት እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸው ቅድመ መስፈርቶች፡

ሁለት መስፈርቶች እስካልተሟሉ ድረስ አምልኮ አላህ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም።

## እነርሱም፡-የመጀመሪያው፡

ኢኽላስ (ስራን ለአላህ ፍፁም ማጥራት)፡ ይህም በስራው የአላህን ፊትና የመጨረሻውን አለም ምንዳ ለማግኘት አስቦ መስራት ነው። የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፡

وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ»،

"አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፤ ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ)"[1] [አል-በይናህ፡ 5].

ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፡-

«إِنَّمَا الْأَعْمَالُ بِالنِّيَّاتِ، وَإِنَّمَا لِكُلِّ امْرِئٍ مَا نَوَى».

"ሥራ የሚለካው በኒያ ብቻ ነው። ሁሉም ሰው (የሚያገኘው) የነየተውን ልክ ነው።"[2]

## ሁለተኛው፡ በንግግርም ይሁን በተግባር ስራችን ነቢዩን

(የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የተከተለ መሆን አለበት። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡

«مَنْ أَحْدَثَ فِي أَمْرِنَا هَذَا مَا لَيْسَ فِيهِ فَهُوَ رَدٌّ»

"በዚህ ጉዳዮችን ከእርሱ ያልሆነን አዲስ መጤ ያመጣ ይዞት የመጣው መጤ ነገር ውድቅ ነው።"[3] ሙስሊም (1718) ላይ ባሰፈሩት ዘገባቸው

«مَنْ عَمِلَ عَمَلًا لَيْسَ عَلَيْهِ أَمْرُنَا فَهُوَ رَدٌّ».

"በርሱ ላይ የኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ነገር የሰራ ሰዉ ስራው ወደርሱ ተመላሽ ነው።"[4]




1- የቁርአን አንቀፁ ትርጓሜም፡ ወደርሱና ወደ አምልኮው በመዞር ከርሱ ውጪ ያሉ አካላትን እንዲተው እንጂ ሌላ አልታዘዙም ማለት ነው። ተፍሲር ሰዕዲይ (ገፅ 538)

2- ቡኻሪ በቁጥር (1) እና ሙስሊም በቁጥር (1907) ዘግበውታል።

3- ቡኻሪ በቁጥር (2697) እና ሙስሊም በቁጥር (1718) ዘግበውታል።

4- ሙስሊም በቁጥር (1718) ዘግበውታል።




# ሁለተኛ፡ የዑምራን አፈፃፀምና ህግጋትን የመማር ብይን፡

አላህን በየትኛውም አምልኮ ሊያመልክ የፈለገ ሰው ስራው ሱናውን የገጠመ እንዲሆንለት በጉዳዩ ላይ የነበረውን የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መመሪያ ሊማር ይገባዋል። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሰዎች የርሳቸውን መመሪያ እንዲከተሉና በርሳቸው መመሪያ እንዲመሩ ያነሳሱ ነበር። ከማሊክ ቢን ሑወይሪሥ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንደተላለፈው እንዲህ አለ፡ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡

«صَلُّوا كَمَا رَأَيْتُمُونِي أُصَلِّي».[5]

"(አሰጋገዴን) ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ስገዱ።"[5]

ከጃቢር (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንደተላለፈው፡ እንዲህ አለ፡

«رَأَيْتُ النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم يَرْمِي عَلَى رَاحِلَتِهِ يَوْمَ النَّحْرِ وَيَقُولُ لِتَأْخُذُوا مَنَاسِكَكُمْ، فَإِنِّي لَا أَدْرِي لَعَلِّي لَا أَحُجُّ بَعْدَ حَجَّتِي هَذِهِ».[6]

"ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) የአርድ ቀን በግመላቸው ላይ ሆነው ጠጠር እየወረወሩ እንዲህ ሲሉ ተመለከትኳቸው "ምንአልባት ከዚህ ሐጄ በኋላ ሌላ ሐጅ ማድረግ መቻሌን አላውቅምና የሐጅና ዑምራ ተግባራችሁን ከኔ ውሰዱ።"[6]

---

2- ቡኻሪ በቁጥር (1) እና ሙስሊም በቁጥር (1907) ዘግበውታል።
3- ቡኻሪ በቁጥር (2697) እና ሙስሊም በቁጥር (1718) ዘግበውታል።
4- ሙስሊም በቁጥር (1718) ዘግበውታል።
5- ቡኻሪ በቁጥር (6008) ዘግበውታል።
6- ሙስሊም በቁጥር (1297) ዘግበውታል።

# ሶስተኛ ፡ የዑምራ ትሩፋት ፡

## ዑምራ ሁለት ትሩፋቶች አሉት ፡ ጥቅል የሆነ እና ልዩ የሆነ ጥቅል የሆነ

### ትሩፋቱ ፡

- ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል ፡ «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል ፡

«الْعُمْرَةُ إِلَى الْعُمْرَةِ كَفَّارَةٌ لِمَا بَيْنَهُمَا، وَالْحَجُّ الْمَبْرُورُ لَيْسَ لَهُ جَزَاءٌ إِلَّا الْجَنَّةَ».[7]

(ከዑምራ እስከ ዑምራ በመካከላቸው የተሰሩትን ወንጀል ማስማሪያ ነው። ተቀባይነት ያለው ሐጅ ለርሱ ከጀነት ውጪ ምንም ምንዳ የለውም።)[7]

---

- ከዐብደላህ ቢን መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ ፡ "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል ፡

«تَابِعُوا بَيْنَ الْحَجِّ وَالْعُمْرَةِ، فَإِنَّهُمَا يَنْفِيَانِ الْفَقْرَ وَالذُّنُوبَ كَمَا يَنْفِي الْكِيرُ خَبَثَ الْحَدِيدِ وَالذَّهَبِ وَالْفِضَّةِ، وَلَيْسَ لِلْحَجِّ الْمَبْرُورِ ثَوَابٌ إِلا الْجَنَّةُ».[8][9]

(ሐጅና ዑምራን አከታትላችሁ አድርጉ። ወናፍ የብረትን፣ የወርቅንና የብርን ቆሻሻ እንደሚያስወግደው እነርሱም ድህነትንና ወንጀልን ያስወግዳሉ። ተቀባይነት ላለው ሐጅ ከጀነት በቀር ሌላ ምንም ምንዳ የለውም።)[8][9]

---

### ልዩ የሆነ ትሩፋቱ ደግሞ በረመዷን ውስጥ ከተደረገ ነው ፡

ከኢብኑ ዓባስ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንደተላለፈው ፡ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል ፡

«عُمْرَةٌ فِي رَمَضَانَ تَقْضِي حَجَّةً مَعِي».[10]

"በረመዷን ውስጥ የሚደረግ ዑምራ ከኔ ጋር እንደሚደረግ ሐጅ ይቆጠራል።"[10]

---

7- ቡኻሪ በቁጥር (1773) እና ሙስሊም በቁጥር (1349) ዘግበውታል።

8- ቲርሚዚይ በቁጥር (810)፣ ነሳኢይ በቁጥር (2631) ዘግበውታል።

9- ብረት ቀጥቃጭና አቅላጭ ብረት የሚያዘጋጅበት እሳት ነው። አትተምሒድ የኢብኑ ዐብዱል በር (15/102)

10- ማለትም ፡ በሌሎች ዘገባዎች እንደተዘገበው ከኔ ጋር ከሚደረግ ሐጅ ጋር እኩል ነው ማለት ነው።

# የዑምራ አፈፃፀም



# የመጀመሪያው፡ የመዋቂት (የኢሕራም ማድረጊያ ስፍራዎች) ህግጋት፡

መዋቂት (የኢሕራም ማድረጊያ ስፍራዎች)፡ ማለት ሐጅ ወይም ዑምራ ማድረግ የፈለገ ሰው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ኢሕራም እንዲያደርግበት የወሰኗቸው ስፍራዎች ናቸው።

ከነዚህ ስፍራዎች መካከል በአንዱ በኩል ሐጅን ወይም ዑምራን ነይቶ የሚያልፍ ሰው ከዛ ስፍራ ኢሕራም ማድረግ ግዴታው ነው። ያለ ኢሕራምም ያንን ስፍራ ማለፍ አይፈቀድለትም።

ከነዚህ ኢሕራም ማድረጊያ ስፍራዎች ይልቅ ወደ መካ ቅርብ የሆነ ሰው የርሱ ኢሕራም ማድረጊያ ስፍራው (ሚቃቱ) ያለበት ስፍራ ነው። ካለበት ስፍራ ሆኖ ሐጅንም ይሁን ዑምራን ኢሕራም ያደርጋል።

የመካ ነዋሪዎችና ከመካ ኢሕራም የሚያደርጉ ሰዎች ለሐጅ ከሆነ ከዛው ከመካ ኢሕራም ያደርጋሉ። ዑምራህ ከሆነ ግን ከሐረም ውጪ ወደሚገኝ ወደ ተንዒምና የመሳሰሉት በመውጣት ኢሕራም ያደርጋሉ።

በአየር የሚሄድ የሆነ ሰው በራሪው ኢሕራም በማድረጊያ ስፍራው (ሚቃቱ) ትይዩ ሲሆን ኢሕራም ያደርጋል። የኢሕራም ማድረጊያ ስፍራውን (ሚቃቱን) ትይዩ ከመሆኑ በፊትም ለኢሕራም ይዘጋጃል። እንዲሁም የኢሕራም ልብስንም ይለብሳል። ልክ በራሪው ከኢሕራም ማድረጊያ ስፍራ (ከሚቃቱ) ትይዩ ሲሆን ወዲያው ኢሕራም ያደርጋል። ከበራሪው እስኪወርድ ድረስ ኢሕራሙን ማዘግየት አይፈቀድለትም። በራሪው ስለሚፈጥን ከኢሕራም ማድረጊያ ስፍራው ኢሕራም ሳያደርግ እንዳያልፍ ከሰጋ በራሪው ኢሕራም ማድረጊያ ስፍራውን ትይዩ ከመሆኑ በፊት ለጥንቃቄ ያህል ተልቢያውን (ለበይከ አልላሁመ ለበይክ) እያለ መጀመር ይችላል።



# ሁለተኛ ፡ የኢሕራም አፈፃፀምና ህግጋት ፡

ኢሕራም ማድረግ ለፈለገ ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መፈፀሙ የተደነገገ ነው ፡

ገላ መታጠብ ፡ ይህም ለወንድም ይሁን ለሴት የወር አበባና የወሊድ ደም ላይ ላለች ሴት ሳይቀር አፅንዖት የተሰጠው ሱና ነው።

---

-ከዑድ ቅባት ወይም ከሌላ ካገኘው ጥሩ መአዛ ካለው ቅባት ጭንቅላቱንና ፂሙን መቀባት። የተቀባው ቅባት ወይም ሽቶ መአዛው ከኢሕራም በኋላ መቅራቱ ምንም ጉዳት የለውም። ሴት ከሆነች ግን ባዳ ወንዶች አንዳያሸቱት ሲባል ሽታ ያለውን ቅባት መቀባት አይፈቀድላትም።



-የኢሕራም ልብስ መልበስ ፡ ይህም ሽርጥና ኩታ ነው። ሱናው ነጫጭና ንፁህ ወይም አዳዲስ መሆናቸው ነው። ሴት ልጅ ግን በጌጥ ያልተገላለጠች ሆና የፈለገችውን ልብስ ለብሳ ኢሕራም ታደርጋለች። ነገር ግን ኒቃብና ጓንት ከመልበስ ትቆጠባለች። ፊቷንና እጇንም ከነዚህ ውጪ ባለ ልብስ ትሸፍናለች።

ግዴታም ይሁን ወይም ሱና የተደነገገ ከሆነ ሶላት ከሰገዱ በኋላ ኢሕራም ማድረግ፤ ግዴታ ግን አይደለም።

(ሉበበይክ አልላሁምመ ዑምራህ) ይላል። ለሌላ ሰው ከሆነ ዑምራ ያደረገው (ሉበበይክ አልላሁመ ዑምረተን ዐን ፉላን) ይላል። ፉላን (እከሌ) በሚለው ፋንታ ዑምራ የሚያደርግለትን ሰው ስም ይተካበት።

ኢሕራም ማድረግ የፈለገ ሰው የሐጅ ወይም የዑምራ ስነ ስርዓቱን አሟልቶ ከመስራት የሚያደናቅፈኝ ነገር ይከሰታል ብሎ ከፈራ ኢሕራም ሲያደርግ (ሉበበይክ አልላሁመ ዑምራህ፣ የሚያግደኝ ነገር ከተከሰተ የኢሕራሜ ፍፃሜ የታገድኩበት ቦታ ነው።) በማለት መስፈርት ማስቀመጥ ይፈቀድለታል። ኢሕራም ሲያደርግ ይህንን መስፈርት ካስቀመጠ በኋላ የሐጁን ወይም የዑምራውን ስነ ስርዓት ከመሙላት የሚያግድ ነገር ከተከሰተ በዛው ወቅት ከኢሕራሙ ይፈታል። ምንም የማድረግ ግዴታም አይኖርበትም።

ከዚያም ተልቢያ አብዝቶ ይበል፡ አባባሉም (ለበይክ አልላሁምመ ለበይክ፣ ለበይክ ላ ሸሪከ ለከ ለበይክ፣ ኢንነል ሐምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላ ሸሪከ ለክ) ወንድ ከሆነ ተልቢያውን ሲል ድምፁን ከፍ ያደርጋል። ሴትም ብትሆን ባዳ ወንዶች ባሉበት ቦታ አስካልሆነች ድረስ ድምጿን ከፍ ታደርጋለች። ኢሕራም ላይ ያለ ሰው ተልቢያ ማብዛት ይገባዋል። በተለይ ሁኔታዎችና ወቅቶች ሲለዋወጡ ለምሳሌ ከፍታ ሲወጣ ወይም ቁልቁለት ሲወርድ ወይም ምሽት ወይም ንጋት ሲደርስ ተልቢያ አብዝቶ ይበል።[11]

በዑምራ ወቅት ኢሕራም ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ጦዋፍ እስኪጀምር ድረስ ተልቢያ ማድረግ የተደነገገ ነው።

11- ሰውዬው (ሉብበይክ) ማለቱ ትርጉሙ፡ ጌታዬ ሆይ! ደግሜ ደጋግሜ ጥሪህን አቤት ብያለሁ። ሃሳቡም ሰውዬው የጌታውን ጥሪ ማክበሩንና ትእዛዙን ፈፃሚ መሆኑን አየገለፀ ነው። "ኢንነል ሐምደ ወንኒዕመተ ለከ ወልሙልክ" (ሐምድ) ማለት ተመስጋኙን ውዴታንና ልቅናን ባቀፈ ምሉዕ ባህሪያት ማውሳት ማለት ነው። ደጋግሞ ካመሰገነ ውዳሴ ይባላል። (ወንኒዕመተ) ማለት አላህ ባሮቹ ፍላጎታቸው እንዲሳካ እና የሚጎዳቸው እንዲወገድ ፀጋውን መዋሉ ነው። (አልሙልክ) ማለት ንግስናም ያንተ ነው። አላህ ተባረከ ወተዓላ ብቻ ነው ንጉሱ ማለት ነው። (ላ ሸሪከ ለክ) ማለት አላህ ብቸኛ በሆነበት ምሉዕ ባህሪያት አንድም የሚጋራው የለም ማለት ነው። አላህ ብቸኛ የሆነበት ሲባልም ለምሳሌ በንግስና፣ በመፍጠር፣ በማስተናበርና በተመላኪነት ያለውን ብቸኝነት ይጠቀሳሉ። ከመጅሙዕ ፈታዋና ረሳኢሉል ዑሠይሚን (22/96) አጠር ተደርጎ የቀረበ።

ኢሕራም ያደረገ ሰው አንድ ሙሕሪም ከኢሕራሙ አስኪፈታ ድረስ የሚከለከላቸው ነገሮችን ከመዳፈር መጠንቀቅ ግዴታው ነው።

# ሶስተኛ ፡ የጦዋፍ አፈፃፀም ፡


ኢሕራም ያደረገ ሰው መስጂደል ሐራም ሲገባ ቀኝ አግሩን ማስቀደሙ ሱና ነው። መስጂድ ሲገባ የሚባለውን ዱዓም ይበል። መስጂድ ሲገባ ከሚባሉ ዱዓዎች መካከል አጅግ የተረጋገጠው ዱዓ "አልላሁምመ - ፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! የአዝነት በርህን ክፈትልኝ" ማለት ነው። ይህን ዱዓ የሚለውም መስጂደል ሐራም ሲገባ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም መስጂድ ሲገባ ነው።

---

ጠዋፍ መጀመር የፈለገ ጊዜ ተልቢያውን ያቋርጣል። "የኢድጢባዕ" አለባበስ ይለብሳል። አለባበሱም ፡ የኩታውን መሃል ቀኝ ብብቱ ስር በመክተት የኩታውን ጫፍ በግራ ትከሻው ላይ ማድረግ ነው። ጦዋፍ አድርጎ አንደጨረሰም ኩታውን ከጦዋፍ በፊት ወደነበረበት አለባበስ ይመልሰዋል። የኢድጢባዕ አለባበስ የሚፈፀመው በጦዋፍ ወቅት ብቻ ስለሆነ ነው።

---

ቀጥሎ ወደ ሐጀረል አስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) ቀደም በማለት በቀኝ አጁ ጥቁሩን ድንጋይ በመዳበስ ይስመዋል፤ መሳሙ ካልገራለት በአጁ ይዳብስና አጁን ይሳም፤ ይህም ካልገራለት በአጁ ሰላም ይለዋል ወይም አንደ ዘንግና የመሳሰሉትን ነገር በመዳበስ ይስመዋል። ይህም ካልገራለት ወደ ሐጀረል አስወድ በመዞር አጁን ወደርሷ በመጠቆም አጁን ሳይስም ያልፋል። ምንም ሳይገፋፋ ሰዎችን ሳያውክና በሰዎች ሳይታወክ መፈፀም በላጭ ነው።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

ሐጀረል አስወድን (ጥቁሩን ድንጋይ) ሲዳብስ ወይም ወደርሱ ሲጠቁም (አላሁ አክበር) ይበል።

---

ከዚያም ቀኝ አቅጣጫን በመያዝ በይተል ሐራምን በግራው በኩል ያደርጋል። ሩክነል የማኒ ጋር ሲደርስም ሳይስመው ይዳብሰዋል። ይህ ካልገራለት ምንም ሳይገፋፋም በእጁም ወደርሱ ሳይጠቁም ያልፋል።

---

በሩክነል የማኒ እና ሐጀረል አስወድ መካከል ሲደርስ (ረብበና አቲና ፊ ዱንያ ሐሰነተን ወፊልአኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበን - ናር) ይበል። ትርጉሙም (ጌታችን ሆይ! በምድረ አለም ደግን ነገር (ፀጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን።) ማለት ነው።

---

በሐጀረል አስወድ በኩል ባለፈ ቁጥር በእጁ ወደርሱ እየጠቆመ (አላሁ አክበር) ይበል።

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

በተቀሩት የጦዋፍ ዙሮች የፈለገውን ዚክር፣ ዱዓና ቁርአን ይበል።


---

ሱናው በሶስቱ የመጀመሪያ ዙሮች ሶምሶማ ማድረግ ነው። ሶምሶማ ማለት፡ እርምጃዎችን ከማቀራረብ ጋር ፈጠን ያለ አረማመድ መራመድ ነው። የተቀሩትን አራት ዙሮች ግን የተለመደውን እርምጃ እንጂ የሚራመደው ሶምሶማ አያደርግም።

---

ጦዋፉን አሟልቶ እንደጨረሰም ወደ መቃም ኢብራሂም በመሄድ ይህንን ይበል፡
﴿وَاتَّخِذُوا مِنْ مَقَامِ إِبْرَاهِيمَ مُصَلًّى﴾،
(ወትተኺዙ ሚን መቃሚ ኢብራሂመ ሙሶላ) ትርጉሙም (ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ።) ማለት ነው። (አል በቀራህ: 125)

ቀጥሎ ከገራለት ሁለት ረከዓን ከመቃሙ ኢብራሂም ኋላ ይሰግዳል። ካልገራለት ደግሞ መስጂዱ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ስፍራ ይሰግዳል። በመጀመሪያው ረከዓ ከፋቲሓ በኋላ፡
﴿قُلْ يَا أَيُّهَا الْكَافِرُونَ﴾
(ቁል ያ አይዩሃል ካፊሩን) ይቀራል። [ሱረቱ አል-ካፊሩን፡ 1] በሁለተኛው ረከዓ ከፋቲሓ በኋላ
﴿قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ﴾.
(ቁል ሁወላሁ አሐድ) ይቀራል። [አልኢኽላስ፡ 1]



# አራተኛ፡ የሰዕይ (በሰፋና መርዋ መካከል የመሮጥ) አፈፃፀም፡

ጠዋፍና ሁለቱን ረከዓዎች ባጠናቀቀ ጊዜ ወደ ሰዕይ ማድረጊያ ስፍራ ይወጣል።

ወደ ሰፋ የቀረበ ጊዜም ይህንን ይበል፡

﴿إِنَّ الصَّفَا وَالْمَرْوَةَ مِنْ شَعَائِرِ اللَّهِ﴾

(ኢንነስ - ሰፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪልሏህ) ትርጉሙም (ሰፋና መርዋ ከአላህ (ትእዛዝ መፈፀሚያ) ምልክቶች ናቸው።) ማለት ነው። (አልበቀራህ፡ 158)

ከዚያም "አላህ ከጀመረበት እጀምራለሁ።" ይላል።

"أَبْدَأُ بِمَا بَدَأَ اللهُ بِهِ".

ከዚያም "አብደኡ ቢማ በደአ' ላሁ ቢሂ" (ትርጉሙ፡ አላህ ከጀመረበት እጀምራለሁ።)[12]



ቀጥሎ ካዕባን መመልከት እስኪችል ወይም ወደ ካዕባ አቅጣጫ ዞሮ ካዕባን እስከሚቀጣጭ ድረስ ወደ ሰፋ ይወጣል። አላህን በመነጠል ተክቢራ ይላል። (ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ላ ኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደህ፣ አንጀዘ ወዕደህ፣ ወነሰረ ዐብደህ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደህ) የሚለውን ውዳሴ ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይበል። በየመሃሉም ዱዓ ያድርግ።

﴿لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْـدَهُ لَا شَرِيـكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْـكُ وَلَهُ الْحَمْـدُ، وَهُـوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيـرٌ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْـدَهُ، أَنْجَزَ وَعْدَهُ، وَنَصَرَ عَبْدَهُ، وَهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ﴾، ثُمَّ دَعَا بَيْنَ ذَلِكَ. قَالَ مِثْلَ هَذَا ثَلَاثَ مَرَّاتٍ.

(ላ ኢላሃ ኢለላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ላ ኢላሃ ኢለላሁ ወሕደህ፣ አንጀዘ ወዕደህ፣ ወነሶረ ዐብደህ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደህ)

12-ሙስሊም በቁጥር (1218) ዘግበውታል።

（ላ ኢላሃ ኢለላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ላ ኢላሃ ኢለላሁ ወሕደሁ፣ አንጀዘ ወዕደሁ፣ ወነሶረ ዐብደሁ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደሁ） （ትርጉሙም፡ ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፤ ለርሱም ተጋሪ የለውም፤ ንግሥናም የርሱ ብቻ ነው፤ ምስጋናም ለርሱ ብቻ የተገባው ነው፤ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፤ ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፤ ብቸኛ አምላክ ነው፤ ቃሉንም ፈፀመ፤ ባርያውንም ድልን አቀዳጀ፤ ብቻውን ሆኖ ስብስቦችን አሸነፈ።） ከዚያም በዚህ መካከል የቻለውን ያህል ዱዓእ ያደርጋል （አላህን ይማጸናል）። ይህንን ዚክር እና ዱዓእ ደግሞ ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይላል።



ቀጥሎ ከሶፋ ወደ መርዋ እየተራመደ ይወርዳል። አረንጓዴው ምልክት ዘንድ ሲደርስም በደንብ ይሮጣል። ሁለተኛው አረንጓዴ ምልክት ዘንድ ሲደርስ የተለመደውን እርምጃ ይራመድ። በደንብ መሮጥ ለሴት ልጅ አልተደነገገላትም።

---

መርዋ ዘንድ የደረሰ ጊዜ ሰፋ ላይ የፈፀመውን አምሳያ ማድረግ ተደንግጎለታል። （ቁጥር ሁለት ላይ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን）

ከዚያም ከመርዋ ወደ ሶፋ እየተራመደ ይውረድ። አረንጓዴው ምልክት ዘንድ የደረሰ ጊዜም በደንብ ይሮጥና ሁለተኛው አረንጓዴ ምልክት ዘንድ የደረሰ ጊዜ የተለመደውን አርምጃ ይራመዳል።

ሰባት ዙር እስኪሞላ ድረስም ልክ በዚሁ መልኩ ይፈፅማል። ከሶፋ ተነስቶ መርዋ እስኪደርስ ያለው ጉዞ አንድ ዙር ይባላል። ከመርዋ ወደ ሶፋ ሲመለስ ደግሞ ሁለተኛ ዙር ይባላል።

ሰዕይ በሚያደርግ (በሚሮጥበት) ጊዜ የፈለገውን ዚክር፣ ዱዓና ቁርአን ይበል።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# አምስተኛ ፡ ፀጉርን የመላጨት ወይም የማሳጠር አፈፃፀም

ዑምራ አድራጊው ጦዋፉንና መሮጡን እንዳሟላ ወንድ ከሆነ ጭንቅላቱን መላጨቱ ወይም ማሳጠሩ ግዴታ ነው። ሱናው መላ ጭንቅላትን መላጨት ወይም ማሳጠር ነው።

---

ዑምራው የተፈፀመው እስከ ሐጅ ባለው ጊዜ ድረስ የጭንቅላት ፀጉር ድጋሚ በማይበቅልበት ልክ በአጭር ወቅት ካልሆነ በቀር መላጨቱ ከማሳጠር በላጭ ነው። እንደዚያ ከሆነ ግን በማሳጠር ላይ ብቻ ይቆጠብ።

---

ዑምራ አድራጊዋ ሴት ከሆነች ከፀጉሯ ጫፍ የጣት ክፋይ ያህል ታሳጥር።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# ኢሕራም ያደረገ ሰው የሚከለከላቸው ነገሮች

## ኢሕራም ላይ ክልክል የሆኑ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው

- ሰውነቱ ላይ የሚገኝን ማንኛውንም ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር፤

- የአግርንም ይሁን የእጅ ጥፍርን ሙሉ ለሙሉም ይሁን የተወሰነውን መቁረጥ፤

- ከጭንቅላት ጋር የሚነካካ በሆነ ነገር ጭንቅላትን መሸፈን፤ ለምሳሌ: ኮፊያና ጥምጣም፣ ኩታን ወይም መሀረቡን ጭንቅላት ላይ ማድረግ ወይም ብርድልብስ ወይም ካርቶንና ከነዚህ ውጪም መሰል ነገሮችን ለጭንቅላት መሸፈኛ የሚታሰቡ ነገሮችን ጭንቅላት ላይ ማድረግ ነው። ይህ ክልከላ ግን ሴቶችን ሳይሆን ወንዶችን ብቻ ነው የሚመለከተው።

- የተለመደውን በሰውነት ልክ ተለክተው የሚዘጋጁ ልብሶችን በተለመደው መልኩ መልበስ ነው፤ ለምሳሌ ያህል ሙሉ የተሰፉ ልብሶች፣ ሱሪ፣ ጃለቢያ፣ ካልሲ፣ ጓንት ይጠቀሳሉ። ይህ ግን ሴቶችን ሳይሆን ወንዶችን ብቻ የሚመለከት ነው። ሴት ልጅ የምትከለከለው: -

- ኒቃብ ወይም ማንኛውም ኒቃብን የመሰሉ ፊት መሸፈኛዎችን መልበስ ነው፤ ባዕድ ወንዶች ፊት ከሆነች ግን መሸፈኛው ከፊቷ ጋር ቢነካካ እንኳ በተለመደው ፊት መሸፈኛ ፊቷን የመሸፈን ግዴታ አለባት። ፊቷን ስትሸፍን ከፊቷ ጋር እንዳይነካካ በሚል ጭንቅላት ማሰሪያ ወይም የመሳሰሉትን መጠቀም አይደነግግላትም። ይህ የተደነገገ መሆኑን የሚጠቁምም ምንም ማስረጃ የለምና።

-አጆቿ ላይ ጓንቶችን ማጥለቅም ትከለከላለች፤ ባዳ ወንዶች ፊት ግን አጆቿን ባባያዋ ውስጥ በመክተት የመሸፈን ግዴታ አለባት።

-በተጨማሪ ኢሕራም ላይ ያለ ሰው ከሚከለከላቸው ነገሮች ሰውነቱን ወይም የኢሕራም ልብሱን ሽቶ መቀባት፤

-የየብስ እንስሶችን አድኖ መግደል ወይም ባይገድሉ እንኳን የማደን ሙከራ ማድረግ፤

-ከራሱም ይሁን ከሌላ ሰው ማጨት፤

-ኒካሕ ማሰር፤

-ከግንኙነት ውጪ ያለ የስሜት መነካካት ለምሳሌ መሳምና በስሜት መተሻሸት፤

-ግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ፤

# የዑምራ ተግባራት ማጠቃለያ (የመጽሐፉ ውጫዊ ልባጅ ላይ ወይም የመጨረሻው ገጽ ላይ ይሆናል)



- ገላ መታጠብ
- ሽቶ መቀባት
- የኢሕራም ልብስ መልበስ
- ኢሕራም አርሱም፡ ወደ ዑምራ ወይም ሐጅ ተግባር መግቢያ ኒያ ነው።
- ተልቢያ
- በአላህ ቤት ጠዋፍ ማድረግ
- ከመቃሙ ኢብራሂም ኋላ ሁለት ረከዓ መስገድ
- በሰፋና መርዋ መካከል መሮጥ
- መላጨት ወይም

ማሳጠር አላህ የበለጠ ዐዋቂ ነው።
የአኳህ ሰላትና ሰላም በነቢያችን
ሙሐመድ ላይ ይስፈን!

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| የዑምራ አፈፃፀምና ህግጋት አጠር ያለ ማብራሪያ | 1 |
| መግቢያ | 3 |
| የመጀመሪያው፡ አምልኮ ተቀባይነት እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸው ቅድመ መስፈርቶች፡ | 4 |
| ሁለተኛ፡ የዑምራን አፈፃፀምና ህግጋትን የመማር ብይን፡ | 5 |
| ሶስተኛ፡ የዑምራ ትሩፋት፡ | 6 |
| የዑምራ አፈፃፀም | 7 |
| የመጀመሪያው፡ የመዋቂት (የኢሕራም ማድረጊያ ስፍራዎች) ህግጋት፡ | 8 |
| ሁለተኛ፡ የኢሕራም አፈፃፀምና ህግጋት፡ | 10 |
| ሶስተኛ፡ የጦዋፍ አፈፃፀም፡ | 12 |
| አራተኛ፡ የሰዕይ (በሰፋና መርዋ መካከል የመሮጥ) አፈፃፀም፡ | 15 |
| አምስተኛ፡ ፀጉርን የመላጨት ወይም የማሳጠር አፈፃፀም | 18 |
| ኢሕራም ያደረገ ሰው የሚከለከላቸው ነገሮች | 19 |
| የዑምራ ተግባራት ማጠቃለያ (የመጽሐፉ ውጫዊ ልባስ ላይ ወይም የመጨረሻው ገጽ ላይ ይሆናል) | 21 |

# تعرف على الإسلام

## بأكثر من 100 لغة

موسوعة القرآن الكريم
QuranEnc.com

ترجمات متقنة لمعاني القرآن الكريم بأكثر من لغة (75)

بيان الإسلام
byenah.com

مواد منتقاة للتعريف بالإسلام وتعليمه بأكثر من (120) لغة

موسوعة الأحاديث النبوية
HadeethEnc.com

ترجمات متقنة للأحاديث النبوية وشروحها بأكثر من (60) لغة

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

مواد منتقاة للحجـــاج والمعتمرين و الزوار بلغات العالم

جامع المحتوى الإسلامي باللغات
islamcontent.com

مواد إسلامية متنوعة وشاملة بأكثر من (125) لغة

موسوعات وخدمات إسلامية باللغات
s.islamenc.com

للمزيد
من المواقع الإسلامية
بلغـــــات العـــالم

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات